# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም

## በረሀብ ከተጠቃው ሕዝባችን ጎን እንቁም፤ እንታደግ

ከ10 ሚሊዮን ያላነሱ ኢትዮጵያውያን ለረሀብ ተጋልጠው ባሉበትና ብዙዎችም--በተለይ ሕፃናት--እየሞቱ እያየን አረመኔው የመለስ ዜናዊ ወያኔ አገዛዝ ረሀቡን ለመደበቅና የተራበውንም ሕዝብ ቁጥር ለማሳነስ ሲፍጨረጨር እየታዘብን ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሕዝብ እየተራበ ምግብ ለውጭ ሀገር ይሸጣል፤ ሕዝብ እየተራበ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ለወያኔያዊ ስብሰባና አስረሽ ምቺ ዛሬም እያጠፋ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ከተራበው ሕዝበ ጎን በመቆም፤ በሁሉም መስክ ለመርዳት በመረባረብ በአቅሙ መታደግ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ እንዳለበት ኢሕአፓ ያሳስባል፡፡

ረሀቡም ሆነ ያለው የኤኮኖሚ ቀውስና ችግር በተፈጥሮ ወይም በውጭ የዓለም ሁኔታ በሚልማጠየቂያ ሊለጠፍ የሚችል ሳይሆን የወያኔ ብልሹ አገዛዝ ውጤት ነው፡፡ የሀገሪቷ ኤኮኖሚ አድጓል ተመንድጓል የሚለው ወያኔ የሚከተለው የመሬትና የእርሻ መንገድ/ፖሊሲ ፀረ እድገትና ፀረ ምርት መሆኑ ያለ ሲሆን በተጨማሪ ሀገሪቷን የወያኔ ኩባንያዎችና የኤኮኖሚ ተቋሞች አለምንም ርህራሄ እየዘረፉ መሆናቸውም መጠቀስ ያለበት ነው፡፡ ከረሀብ አደጋ ለመከላከል አስቀድሞ የማስጠንቀቂያ ሥርዓትን መስርተናል፤ የእህል ጎተራዎች ተበራክተዋል ሲል የነበረው ወያኔ ረሀቡ ሲከሰት ለመደበቅ ከመሞከር የተሻለ እርምጃ ሊወስድ አልቻለም፡፡ ረጂዎችም ወደ ተራበው ሕዝብ አካባቢ እንዳይሄዱ ለማድረግ ሲጥርም ታይቷል፡፡ ይህ ሁሉ ፀረ ሕዝብ እርምጃው መወገዝ ያለበት ሲሆን በሀገራችን በየጊዜው ለሚከሰተው ረሀብ ማስወገጃው በየጊዜው ኡ ኡታ ሳይሆን መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥን በትግላችን ማምጣት መሆኑም ዳግም ግልፅ ሆኗል፡፡ የኑሮ ውድነትና በከተሞችም ሳይቀር ሕዝቡ ለረሀብና አስከፊ ችግር መዳረጉ መፍትሄው ሕዝባዊ ተቃውሞና ዋጋን የሚያስቀንስና አልፎም አረመኔውን አገዛዝ የሚያስወግድ ሕዝባዊ አመፅ መሆኑ መረሳት የለበትም፡፡

የተከሰተውን ረሀብ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያጋለጥን በሌላ በኩል ደግሞ ለተራበው ሕዝብ እርዳታ በቀጥታና በአስተማማኝ መንገድ የሚደርስበትን መንገድ መሻት ግዴታችን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ይህን ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ማጋለጥ፤ ሕዝባዊ አመፅና ትግልን ማደራጀት አለብን፡፡ ሽምቅ ውጊያ በሚካሄድባቸው ቦታዎችም የምግብ እገዳን እንደ መሳሪያ የሚጠቀመውን የወያኔ አገዛዝ ማጋለጥ ይኖርብናል፡፡ የሀገራችንን መሬት ለባዕድ ሰጠ፤ የሀገሪቷን ኤኮኖሚ አድቅቆ ሕዝብን ለረሀብና ለአሰቃቂ ችግር አጋለጠ--ይህንና መሰል የወያኔን ወንጀሎች በግንባር ቀደም እያጋለጥን በዚያውም ፀረ ወያኔ ትግላችንን በማፋፋም ረሀብ የማይከስትባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመመስረት በፅናት እንታገል ሲል ኢሕአፓ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France